159

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ገንዘብ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance

ቁጥር Ref.No. ሃ/ገ/ሐ/5/667
ቀን Date 21/10/2011

ለገቢዎች ሚኒስቴር
<u>አዲስ አበባ</u>

ባለፉት ዓመታት በአገራችን ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት በመከሰቱ እና የብር የመግዛት አቅም ዝቅተኛ እየሆነ በመምጣቱ፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞም በታክሱ ሥርዓት እንዲታቀፉ የማይፈለጉ በርካታ ቁጥር ባላቸው በአነስተኛ ንግድ በተሰማሩ ታክስ ከፋዮች ላይ የወጪ ጫና ለማቅለል ታስቦ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ለተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የተቀመጠው ዓመታዊ ታክሱ የሚከፈልበት የግብይት ዋጋ መጠን ከብር 500 ሺ. ወደ ብር 1 ሚሊዮን ከፍ እንዲል መደረጉ ይታወቃል።

በገዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈፃፀም በወጣው መመሪያ ወኪሉ ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) በላይ ዋጋ ያለው የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ መፈፀም የሚችለው ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከተመዘገቡ ታክስ ከፋዮች ብቻ እንደሆነ የተገለጸው ለተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የተቀመጠው ዓመታዊ ታክሱ የሚከፈልበት የግብይት ዋጋ የገንዘብ መጠን መሻሻልን ተከትሎ ማሻሻያ ያልተደረገበት በመሆኑ በአፈፃፀም ላይ ችግር አስከትሏል። በመሆኑም የገንዘብ መጠን ማሻሻያውን ተከትሎ መመሪያውን ማሻሻል ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል።

ስለዚህ የማሻሻያ መመሪያውን ከዚህ ጋር አባሪ በማድረግ የላክን ስለሆነ ከሰኔ 19 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ እናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

አህመድ ሺዴ
ሚኒስትር

ግልባጭ፣
ለሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
ለታክስ ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት
<u>ገንዘብ ሚኒስቴር</u>

Letter/H/E.T

ስልክ Tel 251- 11- 155 24 00,22 66 98 / 251- 11- 155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905,1037
ፋክስ Fax 251-11-156 01 24,55 14 96 / 251-11-155 11 38
እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa-Ethiopia

## በገዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ
## <u>የወጣውን መመሪያ እንደገና ለማሻሻል የወጣ መመሪያ</u>

በገዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈፃፀም የወጣውን መመሪያ እንደገና ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣ መመሪያው ከዚህ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

### 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "በገዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈፃፀም የወጣውን መመሪያ እንገደና ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. <u>ማሻሻያ</u>

በገዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈፃፀም የወጣው መመሪያ ቁጥር 27/2004 እንደሚከተው እንደገና ተሻሽሏል፡፡

አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1) ተተክቷል፡፡

"5 <u>ታክሱ ተቀናሽ የሚደረግበት ግብይት ዋጋ</u>

1. ወኪሉ ከብር 200,000.00 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) በላይ ዋጋ ያለው የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ መፈፀም የሚችለው ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከተመዘገቡ ታክስ ከፋዮች ብቻ ነው፡፡"

### 3. <u>ማሻሻያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ማሻሻያ ከሰኔ 19 ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ 19 ቀን 2011 ዓ.ም**

**አህመድ ሽዴ**
**የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር**